# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን

### የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የወጪ ንግድ አፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነትን በተመለከተ

### የተከናወነ የክትትል ኦዲት

### /FOLLOW UP AUDIT/ ሪፖርት

መጋቢት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ


የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ)....3

(Executive summary)....3

ክፍል አንድ....5

መግቢያ....5

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ....6

የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ....6

የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች....7

ክፍል ሁለት....8

በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች....8

የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ ለማቆየትና ለማበረታታት የሚያስችል የአሰራር ስርዓትን በተመለከተ፤....8

ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚሆኑ መሬቶችን በማጥናት ለባለሀብቶች ማስተዋወቅን በተመለከተ፤....10

በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ወደልማት ከመግባታቸው በፊት የአዋጭነት ጥናት ማቅረባቸውን በተመለከተ፤....12

ባለስልጣን መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በመተባበር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬት እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች ለባለሀብቶች በወቅቱ እንዲሟሉላቸው የተዘረጋ ስርዓትን በተመለከተ፤....13

አትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ሊይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የኢንሹራንስ...ወዘተ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤....15

ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች በሰው ኃይል እንዲጠናከሩ ማድረጉን በተመለከተ፤....16

የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለሉና ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች በአግባቡና በወቅቱ ለታቀደላቸው አላማ መዋላቸውን በተመለከተ፤....17

ባለስልጣን መ/ቤቱ በአትክልትና ፍራፍሬ በኮንትራት ልማት የሚሳተፉ አርሶ አደሮችን (አውቶግሮዎሮችን) በመመልመል የስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፤....22

የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን ውጤታማ የሚያደርጉ የምርት አመራረትና አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን በመሰብሰብና ማንዋልች በማዘጋጀት በስልጠና እና ሰርቶ ማሳያ ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱን በተመለከተ፤....24

ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶች አለም አቀፍ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችንና ስታንዳርዶችን ያሟሉ መሆናቸውን በተመለከተ፤....25

ባለስልጣን መ/ቤቱ የምርት ግብዓት በወቅቱና በሚፈለገው መጠን እንዲቀርብ ድጋፍና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤ ........ 27
ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች ዕቅድ እና አፈፃፀም ክትትል የሚያደርግ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 28
የባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ላኪ ድርጅቶችና ዩኒየኖች የውጪ ንግድ አፈፃፀም መከታተሉን በተመለከተ፤ ........ 29
ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ማሸጊያ ማቴሪያሎች ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤ ........ 30
ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከመጓጓዛቸው በፊት የሚቆዩበት የማቀዝቀዣ፣ የትራንስፓርትና ሌሎችም የሎጀስቲክስ ፍላጎቶችን እንዲሟሉላቸው ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ፤ ........ 31
የባለስልጣን መ/ቤቱ የገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ተጠቃሚ መሆናቸውን በተመለከተ፤ ........ 32
የሀገሪቱን የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚመለከቱ መረጃዎች በዘመናዊ መልክ የሚደራጁበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 33
ባለስልጣን መ/ቤቱ ዘርፉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፤ ........ 34
የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤትን በተመለከተ፤ ........ 36
የስትራቴጂክ እና ዓመታዊ ዕቅድ እና የዕቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ፤ ........ 36
ክፍል ሦስት ........ 39
የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion) ........ 39
3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው ........ 39
3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው ........ 39
ክፍል አራት ........ 43
የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation) ........ 43

# የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ)

## (Executive summary)

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2006/2007 ዓ.ም በቀድሞ በሆርቲካልቸር ኤጀንሲ በአሁኑ በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የወጪ ንግድ አፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነትን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን ፣ እንዲሁም ባለስልጣን መ/ቤቱ ለመ/ቤታችን የድርጊት መርሀ-ግብር አዘጋጅቶ ባይልክም የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን የክትትል ኦዲት በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት በክትትል ኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው ፡-

- በባለስልጣን መ/ቤቱ ሊዘጋጅ የሚገባው ሁሉን አቀፍ የድጋፍ ማዕቀፍ የአትክልትና ፍራፍሬን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ዋና ዋና የድጋፍ አይነቶችን በዝርዝር በመለየት ድጋፍ የሚሰጠውን አካል ኃሊፊነት፣ ድጋፍ ሊገኝ የሚችልበትን ጊዜ፣ በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ ለማግኘት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር በመለየት ከአንድ መስኮት አገልግሎት(One window shopping) መሰረተ ሀሳብን የሚያመላክት ሁሉን አቀፍ የማበረታቻ የድጋፍ ማዕቀፍ ባለስልጣኑ ያላዘጋጀና በዘርፉ ሊሰማሩ ለሚችሉ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶች እንዲያውቁት የማይደረግ መሆኑ፣
- በአትክልትና ፍራፍሬ የተሰማሩ ባለሀብቶች የሚቀርቡ የአዋጭነት ጥናቶች ደረጃውን የጠበቀ፣ አዋጭነቱ አሰተማማኝ የሆነና ጥናቱ ሊተገበር የሚችል መሆኑ ተገምግሞ እንዲፀድቅ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች መሬት እና የመሰረተ ልማት አገሌግልቶች(መብራት ውኃ፣ ስልክ፣ መንገድ፣ …ወዘተ) በወቅቱ እንዲሟላላቸው አለመደረጉ፣

- አትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የብድር አገልግሎቶች የሚያገኙበት አሰራር ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ለክላስተር የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለሉ ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች በወቅቱ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በውሉ መሰረት የማይሰሩ ባለሀብቶች ላይ እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር አለመዘርጋቱ፣
- በተከታታይ የቴክኖሎጂ ማስረፅ (የሆርቲካልቸር ስራ ዘርፍ በቂ ክህሎትና የስራ ተነሳሽነት በማዳበር ሙያዊ ድጋፍ ከመስጠት አንፃር) የአቅም ግንባታ ድጋፎች በተጠናከረ መልኩ ለባለሀብቱም ሆነ ለአውትግሮዎሩ እንደማይሰጡ እና የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረትና ምርት አያያዝ የአፈፃፀም ማንዋሎች ቢዘጋጁም ተግባራዊ አለመደረጋቸው፣
- የምግብ ደህንነት መስፈርቶችና አለማቀፋዊ ስታንዳርዶች (ግሎባል ጋፕ) ቤንች ማርኮች በባለስልጣን መ/ቤቱ በኩል ለባለሀብቶችም ሆነ ለአውትግሮዎሮች እንዲያውቁት አለመደረጉ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በግብዓት አቅራቢነት የተሰማሩ ኩባንያዎች በማጠናከር ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በዓይነትና በመጠን እንዲቀርቡ ድጋፍና ክትትል እንደማያደርግ እና እጥረት በሚፈጠርበት ወቅት በማስተባበር ችግሩን የሚፈታበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣
- ለሆርቲካልቸር ኤክስፓርት የሚሆኑ አገራዊ የፓኬጂንግ ስታንዳርድ (specification and standard) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- ዘርፉ የሚጠይቀውን አገልግሎት ከማቀላጠፍና ከማሳደግ ረገድ ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር የሌለው መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶች፣ በምርምር ማዕከላትና በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች እንዲጠናከሩ ድጋፍና ክትትል አለማድረጉ፣

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የሆልቲካልቸር ዘርፍ የሚከታተለውና የሚደግፈው አካል ያልነበረውና ነገር ግን በንግድ ሚኒስቴር ስር የኤክስፖርት አፈፃፀም መረጃ የሚመዘግብና ሪፖርት የሚደረግበት አሰራር ብቻ የነበረ ሲሆን ከ 2001 የበጀት ዓመት ጀምሮ የሆልቲካልቸር ልማት ( የአበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ኸርብስ) ዘርፍ ውጤታማነት ወደተሻለ የእድገት ደረጃ ለማሸጋገር እንዲቻል በተሻሻሉ የቴክኖሎጂ ፓኬጆች የታገዘና በግብይት ሰንሰለት ውስጥ የተቀመጡት መስፈርቶችና የተጠቃሚውን ፍላጎት ያሟሉና በአለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ ምርቶች በብዛትና በጥራት ማቅረብ የሚችል የተዋጣለት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለማድረግ የተጠናከረ የፓሊሲ፣ የሙያና አስተዳደራዊ ድጋፍ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ፤ ይህንን ኃላፊነት በባለቤትነት እንዲያስተባብርና እንዲመራ የኢትዮጵያ ሆልቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው በደንብ ቁጥር 152/2008 ተቋቁሟል፡፡

2. የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገት ወደ ኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ለመሸጋገር ድርሻው ከፍተኛ በመሆኑ መንግስት በተቀናጀና በተሳለጠ ሁኔታ ቀጣይነት ያለው ምርትና ምርታማነትን በማሳደግና ፈጣን ዕድገት በማስመዝገብ ኢኮኖሚውን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍና የተያዘውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የአርሶ አደሮችንና የወጣቶችን ቴክኒካል አቅም ከቴክኖሎጂ ጋር ማስተሳሰርና የማይቆራረጥ የማምረት አቅም መገንባት እንዲሁም የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ በኮሜርሻል እርሻዎች ማሳደግ እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በሆርቲካልቸርና በሰፋፊ ኮሜርሻል እርሻዎች ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ለመደገፍ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ እና የግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ እነዚህ ድጋፎች በተናጠል ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ በመሆኑም መንግስት በሁለቱ ተቋማት በተናጠል ሲሰጥ የነበረውን ድጋፍ በተሻለ አቅም ለመደገፍ ሁለቱን ኤጀንሲዎች በአንድ ላይ በማዋሀድ በሚኒስተሮች ምክር ቤት ታህሳስ 21 ቀን ደንብ ቁጥር 396/2009 የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን ተብሎ እንዲቋቋም አድርጓል፡፡

**የክትትል ኦዲቱ ዓላማ**

3. የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2006/2007 ዓ.ም በቀድሞው በሆልቲካልቸር ኤጀንሲ በአሁኑ በኢትዮጵያ ሆልቲካልቸር ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የወጪ ንግድ አፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነትን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን ፤ እንዲሁም ባለስልጣን መ/ቤቱ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ ለመ/ቤታችን የድርጊት መርሀ-ግብር አዘጋጅቶ ባይልክም የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን የክትትል ኦዲት በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ነው፡፡

**የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ**

4. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው ከ2008-2009 ዓ.ም ያሉትን የሁለት በጀት ዓመታት የሥራ ክንውኖችን እንቅስቃሴ መሰረት ባደረገ በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የወጪ ንግድ አፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነት ላይ በተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ለተገኙ ግኝቶች/ግድፈቶች/ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች መተግበራቸውን እና ችግሮቹ መቀረፋቸውን ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲቱ እስከተከናወነበት እስከ 2010 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በባለስልጣን መ/ቤቱ የተከናወኑ ስራዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡
5. የክትትል ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን መ/ቤት እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመረጠው ከታዩ ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሆዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-

መጠይቅ በማቅረብ እና ለክክትል ኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በመከለስና በመተንተን የተካሄደ ነው፡፡

**የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች**

6. የክትትል ኦዲቱን ለማከናወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ናቸው፡፡

# ክፍል ሁለት

## በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች

**የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ ለማቆየትና ለማበረታታት የሚያስችል የአሰራር ስርዓትን በተመለከተ፤**

7. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

8. ባለስልጣን መ/ቤቱ ኢትዮጵያ በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ያላትን አቅምና ተወዳዳሪነት (Comparative advantage) ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እና በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ በክፍለ አህጉር ደረጃ በተለይም በመካከለኛውና ምስራቅ አፍሪካ ውጤታማ የሆኑ አገሮችን ተሞክሮ በመቀመር በዘርፉ ሊሰማሩ የሚችሉ ባለሀብቶችን በተሻለ ለመሳብ የሚያስችል የዘርፉን ልዩ ባህሪያት ያገናዘበ፣ ሁሉን አቀፍ፣ ዘላቂነት ያለው እና አስተማማኝ የድጋፍ ማዕቀፍ (Comprehansive incentive package) ያላዘጋጀና በዘርፉ ሊሰማሩ ለሚችሉ ባለሀብቶችም እንዲያውቁት ያልተደረገ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

9. በባለስልጣን መ/ቤቱ ሊዘጋጅ የሚገባው ሁሉን አቀፍ የድጋፍ ማዕቀፍ የአትክልትና ፍራፍሬን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ዋና ዋና የድጋፍ አይነቶችን ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

10. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

11. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

12. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ዋና ዋና የድጋፍ አይነቶችን ማለትም በግብዓት አቅርቦት ድጋፍ፣ ከምርምርና መሰል ተቋማት በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ፣ በዘር ፍተሻ ማለማመድና ማባዛት ድጋፍ፣ በመሬትና የመሰረተ ልማት አቅርቦት ድጋፍ፣ በብድር አቅርቦትድጋፍ ፣ በውጭ ምንዛሪ አቅርቦትና ዝውውር ድጋፍ፣ በትራንስፖርት ዘርፍ ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ ፣ የአለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ለማሟላት የሚያግዝ የቴክኒክና የስልጠና ድጋፍ፣

13. እንዲሁም ለዘርፉ የሚያስፈልጉ መረጃዎች አቅርቦት እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በመጓጓዝ ሂደት ለሚያጋጥማቸው አደጋና ብልሽት ሊኖር ስለሚችል የዋስትና አቅርቦት ድጋፍ፣ የመሳሰሉ የድጋፍ ዓይነቶችን በዝርዝር በመለየት ድጋፍ የሚሰጠውን አካል ኃላፊነት፣ ድጋፍ ሊገኝ የሚችልበትን ጊዜ፣ በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ ለማግኘት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር በመለየት ከአንድ መስኮት አገልግሎት(One window shopping) መሰረተ ሀሳብን የሚያመላክት ሁሉን አቀፍ የማበረታቻ የድጋፍ ማዕቀፍ ባለስልጣን መ/ቤቱ ያላዘጋጀ መሆኑን ፤

14. በዘርፉ ሊሰማሩ ለሚችሉ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶች እንዲያውቁት አለማድረጉን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

15. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለኢትዮ ቬዥ ፍሩት እና ለመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ስልጠና የሚሰጥ መሆኑን፣ ለተለያዩ ድርጅቶች የድጋፍ ደብዳቤ እንደሚፅፍላቸው እና እርሻቸውን ለማስተዋወቅ አወደርዕዮች /EXHIBITION/ ላይ እንደሚጋብዛቸው፣ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ገለፀዋል፡፡

16. ባለስልጣን መ/ቤቱ የክልል ልማቶችን ተጨባጭ ሁኔታ በገመገመ መልኩ የኤክስፖርት ልማቱን በክልሉ ለመሳብ የሚያስችል የኢንቨስትመንት የማትጊያ ስርዓት ተጠንቶ ክልሉን ባሳተፈ መልኩ ተግባራዊ አለመደረጉን የደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

17. የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንትን ለማቀየት፣ ለመሳብና ለማበረታታት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በፌዴራል ደረጃ ተዘጋጅቶ የወረደ ቢሆንም በተለይ በዞን ደረጃ አከሁን በፊት በተለመደ መልኩ ባለሀብቱ በአትክልትና ፍራፍሬ የዒንቨስትመንት ፈቃድ በማውጣት መሬት ተረክቦ ወደ ስራ ከመግባት ውጪ ሌላ የተዘረጋ የአሰራር ስርዓት አለመኖሩን፣ በተለመደው አሰራር ወደ ስራ የገቡትም ቢሆን ከባንክ ብድር ጋር በተያያዘ በስራው ለመቆየት ችግር እየሆነ እንደሚገኝ

ከጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረጋ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

18. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተደጋጋሚ በህዝብ ክንፍ መድረክ ለሚነሱ የመሰረተ ልማት፣ የገቢያና ሌሎች ችግሮች በሚፈለገው ደረጃ መፍትሔ መስጠት አለመቻሉን፣ አቅም ያላቸውን ባለሀብቶች ወደ ዘርፉ እንዲገቡ ለመሳብ የአቅም ውስንነት መኖሩን፣ ከ 2009 ዓ.ም የባለስልጣን መ/ቤቱ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

19. በ2008 ዓ.ም በአማራና በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎች በተከሰተው የጸጥታ ችግር በተወሰኑ ኩባንያዎች ላይ ጉዳት በመድረሱና በኩባንያዎች የውስጥ መሰረተ ልማት (ጠብታ መስኖ፣ ፓክ-ሀውስ፣ ኮልድ-ሩም፣ ጀነሬተር፣ ስቶር፣ ማሽነሪ፣ ወዘተ) በደረሰው ችግር ኩባንያዎች መዘጋታቸው (ሉና፣ ዘጊቪንግ ትሪ ነርሰሪ፣ ፋንታና ጆቫኒ፣ አልፋኖ ወዘተ) በተመሳሳይ ሁኔታ በተከሰተው የጸጥታ ችግርና ስጋት የሠራተኛ እጥረት ለዘርፉ ዕቅድ አፈጻጸም አሉታዊ አስተዋጽኦ ማሳደሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

20. እንዲሁም አልሜታ ኢምፔክ የተባለ ኩባንያ በተከሰተ የፀጥታ ችግር የመስኖ ውሃ መተላለፊያ መስመር የተቃጠለበት መሆኑ፣ 17 ሄክታር ላይ እሸት ፎሶሊያ ለመትከል አቅዶ እስካሁን ያከናወነው 6 ሄክታር ላይ ሲሆን አፈፃፀሙም 35% መሆኑን፣ ልምድ ያላቸው ሰራተኞች እጥረት ያለበት መሆኑን፣ የመብራት መቆራረጥ ችግር ለተጨማሪ የነዳጅ ወጪ እንደዳረጋቸው፣ ከባለስልጣን መ/ቤቱ የመስክ ክትትል ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

21. ደስታ በርሄ እርሻ የተባለ ኩባንያ በራያ አዘቦ (መሆኒ አከባቢ) የሚገኝ ሲሆን እርሻው ፓክ ሀውስ (የምርት ማቆያ፣ ማቀነባበሪያ፣ የማቀዝቀዣ ማከማቻ) የሌለው መሆኑን፣ ቢሮው የተደራጀ አለመሆኑ፣ በአፈርና በውሃ ናሙና ላይ ተመስርቶ ማዳበሪያ ለሰብሎች የማይሰጥ መሆኑን ከመስክ ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚሆኑ መሬቶችን በማጥናት ለባለሀብቶች ማስተዋወቅን በተመለከተ፤**

22. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

23. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ክልሎች ውስጥ በኦሮሚያ (7293.7ሄ/ር)፣ በአማራ(2662ሄ/ር)፣ በደቡብ ክልል በሀዋሳ አርባ ምንጭ ኮሪድር (1968ሄ/ር)፣ በደቡብ

ትግራይ(ራያና ቆቦ) (1000ሄ/ር) ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተለዩ ቢሆንም ከኦሮሚያ ክልል ውጭ ያሉት የተለዩ መሬቶች በትክክል ለዘርፉ የሚውሉ ስለመሆናቸው በሆርቲካልቸር ኤጀንሲ ጥናት ያልተከናወነ እና መሰረታዊ መረጃዎች ተለይተው ያልተያዙ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

24. ባለስልጣን መ/ቤቱ በየክልሉ የሚገኙ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምቹ የሆኑ መሬቶችን(ማሳዎችን) በመለየት መሰረታዊ መረጃዎችን በማደራጀት ወደ መሬት ቋት እንዲገቡ እና ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ የማስተዋወቅ ስራ ሊሰራ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

25. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

26. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

27. ባለስልጣን መ/ቤቱ በየክልሉ የሚገኙ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምቹ የሆኑ መሬቶችን (ማሳዎችን) በመለየት መሰረታዊ መረጃዎችን በማደራጀት ወደ መሬት ቋት እንዲገቡ እና ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ የማስተዋወቅ ስራ ያልሰራ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

28. በደቡብ ክልል በተወሰኑ ዞኖች ማለትም ሲዳማ፣ጉራጌ፣ጋሞጎፋ ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚሆኑ የኢንቨስትመንት መሬቶች ተዘጋጅተው መረጃው ለባለስልጣን መ/ቤቱ እንደሚሰጥና በዚህም መሰረት ባለሀብቱን የመሳብ ስራ እንደሚሰራ የደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

29. ባለስልጣን መ/ቤቱ የሆርቲካልቸር ዘርፍ ልማትን ለማስፋፋት የመሬት አቅርቦት ችግርን ፈጥኖ መፍታት ያለመቻሉን፣ የዘርፉ የመሰረተ ልማት አገልግሎት አቅርቦት በሚፈለገው ደረጃ አለማሟላቱን ከባለስልጣን መ/ቤቱ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ታውቋል፡፡

በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ወደልማት ከመግባታቸው በፊት የአዋጭነት ጥናት ማቅረባቸውን በተመለከተ፤

30. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

31. የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን መ/ቤት ለአዋጭነት ጥናት የሚያግዙ መረጃዎች በመሰብሰብና በማደራጀት ለባለሃብቶች ያላሰራጨ መሆኑ፣ በተጨማሪም በባለሃብቱ የሚቀርቡ የአዋጭነት ጥናቶችን ለመገምገም የሚያስችል መመሪያና የመገምገሚያ መስፈርት የተዘጋጀ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት 14 የአትክልትና ፍራፍሬ ባለሀብቶች ውስጥ ከአንድ ካምፓኒ (ዩኒ ፍሩት ኃ/የ/የግ/ኩባንያ) በስተቀር በሌሎቹ የአዋጭነት ጥናት ያልቀረቡ መሆኑ፣ እንዲሁም የአዋጭነት ጥናት ያቀረበው ድርጅትም ያቀረበው የአዋጭነት ጥናት ደረጃውን የጠበቀ፣ አዋጭነቱ አስተማማኝ የሆነና ጥናቱ ሊተገበር የሚችል ስለመሆኑ በኤጀንሲው ተገምግሞ የፀደቀ ስለመሆኑ የሚገልፅ መረጃ የካምፓኒው ፕሮፋይል በተከለሰበት ወቅት ያልተገኘ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

32. በአትክልትና ፍራፍሬ የተሰማሩ ባለሀብቶች የአዋጭነት ጥናት እንዲያቀርቡና የሚቀርቡ የአዋጭነት ጥናቶች ደረጃውን የጠበቀ፣ አዋጭነቱ አሰተማማኝ የሆነና ጥናቱ ሊተገበር የሚችል መሆኑ ተገምግሞ ሊፀድቅ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

33. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

34. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

35. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከዞኑ ጋር በመሆን ለአትክልትና ፍራፍሬ አመቺ ቦታዎችን የለየ ቢሆንም የአዋጭነት ጥናቱ ዝርዝር መረጃ ለዞኑ ሳያሳውቅ ለረጅም ዓመት መሬቱ ምንም ጥቅም ሳይሰጥ እንዲቆይ ካደረገ በኋላ መሬቱን እንደማይፈልገው በደብዳቤ የገለፀላቸው መሆኑን፣ ስለዚህም ከዚህ ጋር ተያይዞ በባለስልጣን መ/ቤቱ የተዘረጋ ስርዓት የሌለ መሆኑን የጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች የገለፁ ሲሆን በባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚገኙ የአትክልትና ፍራፍሬ አምራች መካከል

ለክትትል ኦዲት ቡድኑ የቀረበው የ 16 ኩባንያዎች የአዋጭነት ጥናት የተገመገመበት / የተወሰነበት/ ቃለ-ጉባኤ መሆኑ ታውቋል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በመተባበር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬት እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች ለባለሀብቶች በወቅቱ እንዱሟሉላቸው የተዘረጋ ስርዓትን በተመለከተ፤**

36. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

37. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከኦሮሚያ ክልል ጋር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬትና የግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ የሚመቻችበት እና አፈፃፀሙን በቅርበት ክትትል የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ በመተግበር ላይ የሚገኝ ቢሆንም በተለይም በመሬት አቅርቦት በኩል በክልል፣ በዞንና በወረዳ የሚገኙ ኃላፊዎች እርስ በእርስ ተናበውና ተግባብተው የማይሰሩ መሆኑ፣ መመሪያ ሲወጣ ወይም ውሳኔ ሲሰጥ አፈፃፀሙ ደካማ መሆኑ፣ ኤጀንሲው (ከኦሮሚያ ክልል ውጪ) ከሌሎቹ ክልሎች ጋር የጋራ ስምምነት ባለመኖሩ የመሬት አሰጣጥ ሂደቱንና አፈፃፀሙን ክትትልና ድጋፍ የማያደርግ መሆኑን፣ በአጠቃላይ የመሬት አሰጣጥ ስርዓቱ ቀልጣፋ አለመሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

38. በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች መሬት እና የመሰረተ ልማት አገሌግልቶች(መብራት ውኃ፣ ስልክ፣ መንገድ፣ ...ወዘተ) በወቅቱ ሊሟሉላቸው እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

39. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

40. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

41. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች መሬት እና የመሰረተ ልማት አገልግልቶች(መብራት፣ ውኃ፣ ስልክ፣ መንገድ፣ወዘተ...) በወቅቱ እንዲሟላላቸው እንደማያደርግ ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ

ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

42. የኢትዮ ቬዥ ፍሩት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ባለስልጣን መ/ቤቱ አስፈላጊውን ፈቃድ ለማግኘት የትብብር ደብዳቤ እንደሚፃፍላቸው የገለፁ ሲሆን የደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በበኩላቸው ለአትክልትና ፍራፍሬ የሚዘጋጁ መሬቶች ለፕሮጀክቱ መዳረሻ መንገድ እና ሌሎች የመሰረተ ልማት አውታሮች የሌላቸው ከሆነ የባለሀብቱን እንቅስቃሴ መነሻ በማድረግ ለሚመለከታቸው አካላት የድጋፍ ደብዳቤ እንደሚፅፉ እና ክትትል እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

43. ከመሰረተ ልማት ጋር በተያያዘ በተወሰኑ ፕሮጀክቶች ላይ የተሰራ ቢሆንም በአብዛኛው ችግር ያለ መሆኑን፣ ለምሳሌ በአልግሪን አግሮ ኢንዱስትሪ ብቻ ዞኑ ከክልሉ ጋር በመሆን የ 50 ኪሎ ሜትር መንግድ የሠራ መሆኑን፣ ነገር ግን ከመብራት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ችግር ያለ መሆኑን የጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

44. ጂጂ ኮታሪ በሱሉልታ የሚገኝ እርሻ ሲሆን የመብራት ሃይል መቆራረጥ እንዲሁም መጥፋት ምክንያት በወር ለ 400 ሊትር የነዳጅ ወጪ መዳረጋቸውን፣ ካርጎ ላይ ምርታቸው በሚገባው የሙቀት መጠን/ በ 2 ዲግሪ ሴንቲግሬድ/ አለመቀመጥ እና አለመጫን፣ በሀገር ውስጥ ያሉት ኬሚካል አቅራቢዎች ፒ ኤች አይ ከ 1-3 ቀናት የሆኑ ኬሚካሎችን ማቅረብ አለመቻላቸውን፣ ድሬ ሀይላንድ የተባለው እርሻ የሚገኘው በሆለታ ሲሆን አጠቃላይ የመሬት ይዞታው 50 ሄ/ር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 5.75 ሄ/ር /11.5%/ መሬት በአልቢዮን ዝርያ እንጆሪ ለምቶ የሚገኝ መሆኑን፣ ኩባንያው የኤሌክትሪክ ሃይል መቆራረጥ እና መጥፋት ችግር ያለበት ሲሆን ጀነሬተርም የሌለው መሆኑን ፣

45. እንዲሁም ጂቱ ሃዋሳ ጥቁር ውሃ ኩባንያ የኤሌክትሪክ ሃይል መቆራረጥ እና መጥፋት ችግር ያለበት መሆኑን፣ በሳምንት ለ 15 ሰዓት ያህል የመብራት መጥፋትና መቆራረጥ ምክንያት በየሳምንቱ 6000 ብር ለነዳጅ ወጪ መዳረጋቸውን ፣

46. በተጨማሪም ጆይ ቴክ የተባለ እርሻ የሚገኘው በደብረዘይት ሲሆን የኤሌክትሪክ ሃይል አለመኖሩን ፣ ግሪን ማርክ ኸርብስ ኩባንያ የመብራት መጥፋት ችግር ያለበት

መሆኑ፣ በዚህም ምክንያት ለጀነሬትር ነዳጅ በወር 37,850 ብር ወጪ መዳረጋቸውን እና ፍሬዚያ የተባለ ኩባንያ የሚገኘው በሱሉልታ ሲሆን የኤሌክትሪክ መቆራረጥ ችግር ምክንያት በወር ለጄነሬተር ነዳጅ በወር እስከ 25,000 ብር ተጨማሪ ወጪ መዳረጋቸውን ከመስክ የክትትል ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

**አትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ሊይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የኢንሹራንስ...ወዘተ አገልግልቶችን እንዲያገኙ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤**

47. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

48. በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሃብቶች በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚሰጠው አገልግሎት ቀልጣፌ ያለመሆኑ፣ የሀገሪቱ የውጪ ምንዛሬ እድገት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ትላልቅ ባለሀብቶች(ሞዴል የሆኑ የአትክልትና ፍራፍሬ ኩባንያዎች) ተለይተው የሚስተናገዱበት አሰራር ያለመኖሩ፣ የልማት ባንክ ከሌሎች ባንኮች ጋር ተቀናጅቶ የማይሰራና የብድር ጥያቄ ሲቀርብ ለመወሰን ረጅም ጊዜ የሚወስድ መሆኑ፣ እንዲሁም በባንክና ጉምሩክ መካከል የሚካሄደው የኤክስፖርት መረጃ ፍሰት ወቅታዊ፣ ተመሳሳይ፣ ትክክለኛና ያልተሟላ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

49. አትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የብድር አገልግሎቶች የሚያገኙበት አሰራር ሊዘረጋ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

50. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

51. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

52. ባለስልጣን መ/ቤቱ አትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የብድር አገልግሎቶች የሚያገኙበት አሰራር ያልዘረጋ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች

የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች የገለፁ ሲሆን ኢትዮ ቬ'ዥ ፍሩት እርሻ ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች አስፈላጊውን ትብብር ለማግኘት የትብብር ደብዳቤ እንደሚፅፍላቸው ገልፀዋል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች በሰው ኃይል እንዲጠናከሩ ማድረጉን በተመለከተ፤**

53. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

54. ባለስልጣን መ/ቤቱ ድርጅቶች ለልማቱ የሚያስፈልጋቸውን የሰው ኃይል በማስተባበርና በሚሟላት ድጋፍ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

55. የአትክልትና ፍራፍሬ ልማቶችን በሰው ኃይል እንዲጠናከሩ በባለስልጣን መ/ቤቱ ድጋፍና ክትትል የሚደረግበት አሰራር ሊዘረጋ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

56. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

57. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

58. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከፌዴራልና ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ጋር የስራ ግንኙነት በመፍጠር አትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች በሰው ኃይል እንዲጠናከሩ ድጋፍና ክትትል የሚደረግበት አሰራር ያልዘረጋ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

59. ባለስልጣን መ/ቤቱ ሳይሆን ክልሉ በሁሉም የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በተለይ በአረም እና ምርት አሰባሰብ ወቅት ላይ ባለሀብቶች በሚያጋጥማቸው የጉልበት ሰራተኝ እጥረት ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ድጋፍ እንዲያደርግላቸው የድጋፍ ደብዳቤ የሚፅፉላቸው መሆኑን የደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

60. የኢትዮ ቬዥር ፍሩት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ባለስልጣን መ/ቤቱ ለባለሞያዎቻቸው ስልጠና በየመስኩ እንደሚሰጣቸው እንዲሁም ለመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር ሞያተኞች ስልጠና እንደሚሰጥ፣ የሰው ሀብት ልማት ላይ ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋር በማስተሳሰር ተጨማሪ የሰው ሀይል እንዲቀጠር ትብብር እንደሚደረግ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ አስረድተዋል፡፡

**የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለሉና ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች በአግባቡና በወቅቱ ለታቀደላቸው አላማ መዋላቸውን በተመለከተ፤**

61. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

62. ከ2003-2006 ዓ.ም በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ከተሰማሩ 38 ባለሀብቶች ውስጥ 11 ባለሀብቶች ወደ ልማት ያልገቡ መሆናቸው፣ 17 ባለሀብቶች የሚያመርቱትን ምርት ለውጪ ገበያ የማያቀርቡ መሆናቸው፣ አጠቃላይ በአትክልትና ፍራፍሬ ለባለሀብቶች ከተላለፈ መሬት (16,756 ሄክታር) የለማው እስከ 2006 ዓ.ም 11,517 ሄክታር (69%) ብቻ መሆኑ፣ ለሙዝ አአውት ግሮዎር አምራቾች 10,000 ሄክታር መሬት ሁለም የሚለማ ቢሆንም የሙዝ ምርት ለውጪ ገበያ የማይቀርብ መሆኑ እንዲሁም ወደ ልማት ከገቡት 27 ባለሀብቶች ውስጥ ደግሞ 17 ባለሀብቶች የሚያመርቱትን ምርት ለውጪ ገበያ የማያቀርቡ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

63. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለክላስተር የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለለ ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች በወቅቱ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በውሉ መሰረት የማይሰሩ ባለሀብቶች ላይ እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር ሊዘረጋ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

64. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

65. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

66. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለክላስተር የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለለ ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች በወቅቱ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በውሉ መሰረት የማይሰሩ ባለሀብቶች ላይ እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር ያልዘረጋ

መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

67. በዞኑ በኢንቨስትመንት ለተሰማሩ ማለትም በሶስት ዘርፍ / ግብርና፣አገልግሎት እና ኢንዱስትሪ/ በአንድ ላይ ከመከታተል ውጪ የተለየ ለአትክልትና ፍራፍሬ ብቻ የተዘረጋ የክትትል የአሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑን የጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

68. አልሜታ ወንዶ ጢቃ እርሻ ልማት ኩባንያው የሚገኘው በዶሬ ባፈና ክ/ከተማ ሰማ ኤጀርሳ ቀበሌ ውስጥ ሲሆን ውል የገባው 23/11/2004 ዓ.ም መሆኑ፣ መጀመሪያ የተረከበው የመሬት መጠን 500 ሄ/ር ሲሆን የተሰማራበት የሥራ መስክ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ሲሆን በኢንቨስትመንት ፈቃዱ መሰረት ማልማት ያልጀመረ መሆኑን፣ ኩባንያው በኢንቨስትመንት ፈቃዱ መሰረት አትክልትና ፍራፍሬ ሳይሆን በየምርት ዘመኑ በቆሎ እያመረተ እንደሚገኝ፣ እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ አቶ ቴዎድሮስ ታደሰ ኩባንያ የሚገኘው ቱላ ክ/ከተማ ዳቶ ቀበሌ ውስጥ ሲሆን የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ውል የገባው በ 06/06/2005 ዓ.ም መሆኑ፣ የተረከበው መሬት መጠን 21 ሄ/ር ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ከኢንቨስትመንት ፈቃዱ ውጪ በቆሎ እያመረተ እንደሚገኝ ከሀዋሳ ከተማ ኢነቨስትመንት ኮሚሽን የመስክ ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡



ምስል፡-1 አልሜታ ወንዶ ጢቃ እርሻ ለአትክልትና ፍራፍሬ ለማልማት መሬት ተረክቦ በቆሎ የተዘራበት

69. በ 2009 ዓ.ም በአትክልት፣ ፍራፍሬና ኸርብስ በ 34 ባለሀብቶች የለማ መሬት በሂ/ር 2,152.76 መሆኑ፣ ከዚህ ውስጥ በምርት የተሸነ መሬት በሂ/ር 1,007.72 ሲሆን ጥቅም ላይ ያልዋለ መሬት መጠን በሂ/ር 1,288.39 ወይም 59% መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

70. መሀመድ ኢብራሂም ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ ኢታምኮ ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ ጂ ጂ ኮታሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ ሃድያ ፍላወር ኃ/የተ/የግል ማህበር የተባሉ ኩባንያዎች ባቀረቡት የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት የወሰዱትን መሬት ሙሉ ለሙሉ ባለማልማታቸውና የውጪ ንግድ /ኤክስፖርት/ ድርሻቸውን ባለማሳደጋቸው በ 2007 ዓ.ም የመስጠንቀቂያ ደብዳቤ የተፃፈላቸው ቢሆንም ኩባንያዎቹ ችግሩን ባለመቅረፋቸው ባለስልጣን መ/ቤቱ በድጋሚ በ2008 ዓ.ም የማስጠንቀቂያ በደብዳቤ የፃፈላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

71. ኤስ ኤም አር የተባለ እርሻ የሚገኘው በደብረዘይት ሲሆን ኩባንያው በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ልማቱን እየሰራ እንደማይገኝ፣

72. ኦክሊፍ የተባለው እርሻ የሚገኘው በሆለታ አዲስ አለም ሲሆን ኩባንያው ከ 6 ወር በፊት ስራ ያቆመ መሆኑን እና በአሁኑ ሰዓት ኩባንያው ላይ ከጥበቃ ሰራተኞች በስተቀር ምንም እንቅስቃሴ የሌለ መሆኑን፣

73. ጋሎብ አግሮ ኢንዱስትሪ እርሻ በሰገን ዞን በአማሮ ክሌ ወረዳ በአቡሎ ክሌ ወረዳ በአቡሎ አልፋጮ ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን አጠቃላይ ይዞታው 2792 ሄ/ር መሆኑ፣ ከዚህ ውስጥ 500 ሄ/ር በሙዝ ለመሸፈን አቅዶ እስከአሁን 14 ሄ/ር / የዕቅዱን 2.5% / ያለማ መሆኑን፣ የመብራት ችግር ስላለባቸው በአጠቃላይ በጀነሬተር የሚጠቀሙ መሆኑን ፣

74. በአርባምንጭ የሚገኘው ሉሲ የእርሻ ኩባንያ አጠቃላይ የእርሻው ስፋት 1500 ሄ/ር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 36 ሄ/ር ለተለያዩ መሰረተ ልማት ሲውል የተቀረው 1464 ሄ/ር መሬት በተለያዩ ሰብሎች ሊሸፈን የሚችል መሬት ሲሆን ከዚህ መሬት ውስጥ 600 ሄ/ር ሙዝ የተሸፈነና 12.5 ሄ/ር በማንጎ/ አፕል ማንጎ/ ሰብል ሲሸፈን 851.5 ሄ/ር /58%/ ሄ/ር ያለማ መሆኑን፣

75. ጂቱ የተባለ እርሻ የሚገኘው በደብረዘይት ሲሆን ካለው አጠቃላይ 70 ሄ/ር መሬት ውስጥ ሊለማ የሚችለው መሬት 52 ሄ/ር ሲሆን 2 ሄ/ር ግሪን ሀውስ/ፕሮፖጌሽን እና ፓፕሪካ/ እየለማበት ሲሆን በመስክ ላይ ጎመን /ብሮኮሊና 5.8 ሄ/ር፣ የአበባ ጎመን 3.7 ሄ/ር፣ የተለያዩ ሰላጣዎች / ሎሎ ሮሶ 2.2 ሄ/ር፣ ኦክሊፍ 2.2 ሄ/ር፣ ፍሬዚያ ግሪን 1.2 ሄ/ር፣ አይስ በርግ 1.6 ሄ/ር / ፣ ፈነል 2.3 ሄ/ር ፣ ኩኹት 0.8 ሄ/ር፣ ፓፕሪካ 1 ሄ/ር ለምቶ የሚገኝ መሆኑ እና አጠቃላይ ያለማው መሬት 22.8 ሄ/ር ሲሆን 29.2 ሄ/ር /56%/ መሬት ያላለማ መሆኑ፣ የካንፓኒው ኤክስፖርት ገበያቸው ዱባይ እና ናይጄሪያ ሲሆን ግሎባል ጋፕ ኦዲት አለመደረጋቸውን፣

76. ረይን ባው ክለርስ የተባለ ኩባንያ የሚገኘው በደብረዘይት ሲሆን የተለያ አትክልቶችን ለማልማት ካለው አጠቃላይ መሬት ውስጥ 18 ሄ/ር ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚውል 3 ሄ/ር ቲማቲም እና 2 ሄ/ር ቃርያ / 27 % / ብቻ እያለማ የሚገኝ መሆኑን ፣

77. ጂቱ ቆቃ የተባለ ኩባንያ ምንም ዓይነት እንቅስቀሴ ያልጀመረ መሆኑን፣

78. ኢትኮ የተባለ ኩባንያ ለረጅም ጊዜ ስራ ያቆመ መሆኑን፣

79. ቲናው ቢዝነስ ግሩፕ ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በወሰደው መሬት ላይ ምንም አይነት ልማት ያላከናወነ መሆኑን፣

80. ሳቫና እርሻ የተባለ ኩባንያ በራያ አዘቦ ( መሆኒ አከባቢ) የሚገኝ ሲሆን ለኤክስፖርት ሊሆኑ የሚችሉ ሰብሎችን ሳይሆን ከሆርቲካልቸር ውጪ የሆኑ ሰብሎችን እየሰራ መሆኑን፣ እንደ (ጤፍ፣ በቆሎ፣ ሽንኩራ ወዘተ…)፣ ዘመናዊ የሆነ የማዳበሪያ እና የውሃ አጠጣጥ ቴክኖሎጂ አለመጠቀሙ፣ ኩባንያው በሚጠበቀው ደረጃ ጥራት ባለው መልኩ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ያልቻለ መሆኑን ፣

81. ጠለታ የተባለው ኩባንያ በጠቅላላ 12 ሄ/ር መሬት ሲኖረው በክረምት በቆሎ የተዘራበትና አሁን ምንም ሰብል የሌለው ቦታ መኖሩን፣

82. ተክለድብ የተባለ ኩባንያ 16 ሄ/ር መሬት ይዞታ ሲኖረው ቦታው ምንም ዓይነት ሰብል የሌለው መሆኑን፣

ከባለስልጣን መ/ቤቱ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እና የመስክ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

83. ከ 2008 ዓ.ም የመሬት አጠቃቀም ግምገማ ለመረዳት እንደተቻለው ፡-

84. በሆለታ ልማት ክላሰተር ውስጥ በቁጥር 7 በአትክልት ፍራፍሬን ሀርብስ የተሰማሩ ኩባንያዎች ያሉ ሲሆን አጠቃላይ የመሬት ይዞታቸው 191 ሄክታር መሆኑ፣ ከጠቅላላው የመሬት ስፋት ውስጥ ስፋቱ 122 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአትክልት ፍራፍሬ መሰረተ ልማት የተሸፈነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 69 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአግባቡ ለልማት ያልዋለ መሆኑን፣

85. በሰበታ ልማት ክላሰተር ውስጥ በቁጥር 2 በአትክልት ፍራፍሬን ሀርብስ የተሰማሩ ኩባንያዎች ያሉ ሲሆኑ አጠቃላይ የመሬት ይዞታቸው 43 ሄክታር መሆኑ፣ ከጠቅላላው የመሬት ስፋት ውስጥ ስፋቱ 10 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአትክልት ፍራፍሬ መሰረተ ልማት የተሸፈነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 33 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአግባቡ ለልማት ያልዋለ መሆኑን ፣

86. በመርቲ ልማት ክላሰተር ውስጥ በቁጥር 10 በአትክልት ፍራፍሬን ሀርብስ የተሰማሩ ኩባንያዎች ያሉ ሲሆኑ አጠቃላይ የመሬት ይዞታቸው 1286 ሄክታር መሆኑ፣ ከጠቅላላው የመሬት ስፋት ውስጥ ስፋቱ 325 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአትክልት ፍራፍሬ መሰረተ ልማት የተሸፈነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 961 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአግባቡ ለልማት ያልዋለ መሆኑን፣

87. በቢሾፍቱ ልማት ክላሰተር ውስጥ በቁጥር 1 በአትክልት ፍራፍሬን ሀርብስ የተሰማራ ኩባንያ ያለ ሲሆን አጠቃላይ የመሬት ይዞታው 20 ሄክታር መሆኑ፣ ከጠቅላላው የመሬት ስፋት ውስጥ ስፋቱ 18 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአትክልት ፍራፍሬ መሰረተ ልማት የተሸፈነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 2 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአግባቡ ለልማት ያልዋለ መሆኑን፣

88. በወሊሶ ልማት ክላሰተር ውስጥ በቁጥር 1 በአትክልት ፍራፍሬን ሀርብስ የተሰማራ ኩባንያ ያለ ሲሆን አጠቃላይ የመሬት ይዞታው 30 ሄክታር መሆኑ፣ ከጠቅላላው የመሬት ስፋት ውስጥ ስፋቱ 12 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአትክልት ፍራፍሬ መሰረተ ልማት የተሸፈነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 18 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአግባቡ ለልማት ያልዋለ መሆኑን፣

89. በኤጀሬ ልማት ከላሰተር ውስጥ በቁጥር 1 በአትክልት ፍራፍሬን ሀርብስ የተሰማራ ኩባንያ ያለ ሲሆን አጠቃላይ የመሬት ይዞታው 33.5 ሄክታር መሆኑ፣ ከጠቅላላው የመሬት ስፋት ውስጥ ስፋቱ 13.5 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአትክልት ፍራፍሬ መሰረተ ልማት የተሸፈነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 20 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአግባቡ ለልማት ያልዋለ መሆኑን፣

90. በቆቃ ልማት ከላሰተር ውስጥ በቁጥር 8 በአትክልት ፍራፍሬን ሀርብስ የተሰማሩ ኩባንያዎች ያሉ ሲሆን አጠቃላይ የመሬት ይዞታቸው 675 ሄክታር መሆኑ፣ ከጠቅላላው የመሬት ስፋት ውስጥ ስፋቱ 344 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአትክልት ፍራፍሬ መሰረተ ልማት የተሸፈነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 331 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአግባቡ ለልማት ያልዋለ መሆኑን፣

91. በሱሉልታ ልማት ከላሰተር ውስጥ በቁጥር 2 በአትክልት ፍራፍሬን ሀርብስ የተሰማሩ ኩባንያዎች ያሉ ሲሆን አጠቃላይ የመሬት ይዞታቸው 49 ሄክታር መሆኑ፣ ከጠቅላላው የመሬት ስፋት ውስጥ ስፋቱ 14 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአትክልት ፍራፍሬ መሰረተ ልማት የተሸፈነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 35 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአግባቡ ለልማት ያልዋለ መሆኑን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ በአትክልትና ፍራፍሬ በኮንትራት ልማት የሚሳተፉ አርሶ አደሮችን (አውቶግሮዎሮችን) በመመልመል የስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፤**

92. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

93. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኤክስፖርት ምርት ማምረት የሚችሉ የኮንትራት አርሶ አደሮችን (አውትግሮዎሮችን) ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ምቹ በሆኑ ክልሎች እንዲደራጁና ወደ ምርት እንዲገቡ እና ተከታታይነት ያለው የክህሎት ስልጠናዎችና የቴክኒክ ድጋፎችን በመቂ አካባቢ ላሉ አውትግሮዎሮች የሚያደርግ ቢሆንም በሌሎቹ አካባቢዎች ያልተስፋፋ መሆኑ፣ እንዲሆም የኮንትራት አርሶ አደሮች (አውትግሮዎሮች) ማበረታታት የሚችሉ የግብይት፣ የብድርና የሎጀስቲክስ መሰረተ

ልማት አገልግልቶች እንዲሟሉላቸው በበቂ ሁኔታ ድጋፍና ክትትል የማያደርግ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

94. ባለስልጣን መ/ቤቱ በሆርቲካልቸር ልማት የሚሰማሩ አውትግሮዎሮች እንዲደራጁ ሊያደርግ እና አውትግሮዎሮቹና አምራቾች በቂና ተከታታይነት ያለው የክህሎት ስልጠናዎች እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

95. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት  የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

96. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

97. ባለስልጣን መ/ቤቱ በሆርቲካልቸር ልማት የሚሰማሩ አውትግሮዎሮች እንዲደራጁ ያላደረገ እና አውትግሮዎሮችና አምራቾች በቂና ተከታታይነት ያለው የክህሎት ስልጠናዎች እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል የማያደርግ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ  ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

98. በባለስልጣን መ/ቤቱ ለባለሀብቶችና ለገበሬዎች ልማት ላይ የመስኖ አጠቃቀም፣ የአግሮኖሚ እንክብካቤ፣ ዝርያ አመራረጥ፣ ምርት አጠባበቅና ሌሎች የአትክልትና ፍራፍሬ ቴክኖሎጂ ፓኬጅ ያካተተ የሙያ ማሻሻያ አውደ ጥናትና ስልጠና ተዘጋጅቶ የማይሰጥ መሆኑን፣ ከክልሎች ጋር በመተባባር በአትክልትና ፍራፍሬ በኮንትራት ልማት የሚሳተፉ አርሶአደሮች(አውትግሮወሮች) በመመልመል  እንዲደራጁ ያላደረገ እና ለኮንትራት አርሶአደሮችና ለክልል ባለሞያዎች የስልጠናና የቴክኒክ ድጋፍ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑን ከደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና ከጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

99. የቆቃ ቬጅ አውትግሮወር ስኪም አከባቢ አርሶ አደሮች የእውቀትና የክህሎት ክፍተት ያለባቸው መሆኑ፣ እንዲሁም በአከባቢው ላይ ከዚህ በፊት የማይታወቅ በመሆኑና ለኤክስፖርት የሚሆኑ ሰብሎች ላይ ከፍተኛ የግንዛቤና የዕውቀት ክፍተት ያለ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

**የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን ውጤታማ የሚያደርጉ የምርት አመራረትና አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን በመሰብሰብና ማንዋልች በማዘጋጀት በስልጠና እና ሰርቶ ማሳያ ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱን በተመለከተ፤**

100. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

101. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት አመራረትና ምርት አያያዝ የስልጠና ማንዋሎች የተዘጋጁ ቢሆንም ተግባራዊ እንዲሆኑ የስልጠናና የግንዛቤ ስራዎች በስፋት ባለመከናወናቸው በአርባምንጭና በድሬዳዋ የልማት ኮሪደር የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት አሰባሰብና አያያዝ በአውትግሮዎሩም ሆነ በባለሀብቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ሳይንሳዊ ሂደትን የተከተለ አለመሆኑ ታውቋል፡፡ለምሳሌ ስለ አመራረት ሂደት፣ ድህረ-ምርት አሰባሰብና አያያዝ፣ የምርት ማጠራቀሚያ፣ የምርት አስተሻሸግ፣ የምርት ማጓጓዝ ዘዴ፣ የኬሚካል አጠቃቀምና አያያዝ ባህላዊና ኃላቀር በመሆኑ እና የግንዛቤ እጥረት መኖሩ፣ በመድኃኒት ርጭት ወቅት የሚደረግ የግል ደህንነት (personal safety) የማያደርጉ መሆኑ እንዲሁም ኤጀንሲው በበሽታና ተባይ መካላከል በወረርሽኝ መልክ ካልተከሰተ በስተቀር ለቅድመ ጥንቃቄ የሚረዱ ሙያዊ እገዛ የማይደረግ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

102. በተከታታይ የቴክኖሎጂ ማስረፅ (የሆርቲካልቸር ስራ ዘርፍ በቂ ክህሎትና የስራ ተነሳሽነት በማዳበር ሙያዊ ድጋፍ ከመስጠት አንፃር) የአቅም ግንባታ ድጋፎች በተጠናከረ መልኩ ለባለሀብቱም ሆነ ለአውትግሮዎሩ ሊሰጥ እንደሚገባ እና የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረትና ምርት አያያዝ የአፈፃፀም ማንዋሎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ሊደረጉ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

103. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

104. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

105. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተከታታይ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን ውጤታማ የሚያደረጉ የቴክኖሎጂ ማስረፅ (የሆርቲካልቸር ስራ ዘርፍ በቂ ክህሎትና የስራ ተነሳሽነት በማዳበር ሙያዊ ድጋፍ ከመስጠት አንፃር) የአቅም ግንባታ ድጋፎች በተጠናከረ መልኩ ለባለሀብቱም ሆነ ለአውትግሮዎሩ ያልሰጠ መሆኑን እንዲሁም የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረትና ምርት አያያዝ የአፈፃፀም ማንዋሎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ አለመደረጋቸውንከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

106. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለባለሀብቱም ሆነ ለአውትግሮዎሩ በተከታታይ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን ውጤታማ የሚያደረጉ የቴክኖሎጂ ማስረፅ ፣ የአቅም ግንባታ ድጋፎች ዙርያ ምንም ስራ ያላከናወነ መሆኑን ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረትና ምርት አያያዝ የአፈፃፀም ማንዋሎች በማዘጋጀት ስልጠና አለመስጠቱ እንዲሁም ወደ አርሶ አደሩ መውረዱን የሚረጋገጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን ከደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና ከጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

107. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአካባቢ ጥበቃና ማህበራዊ ተጽዕኖ ዙሪያ የተሰሩ ምርጥ ተሞክሮዎችን ቀምሮ ማስፋት ላይ ውስንነት እንዳለበት እና በመስክ ላይ ተገኝቶ የባለሀብቱን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ እና ውጤት ያመጡ ተግባራት ላይ ማትኮር ጉድለት እንዳለበት ከተከለሱ ማስረጃዎች ታውቋል፡፡

**ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶች አለም አቀፍ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችንና ስታንዳርዶችን ያሟሉ መሆናቸውን በተመለከተ፤**

108. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

109. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች ኤክስፖርት የሚያደርጓቸው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች የምግብ ደህንነት መስፈርቶችና አለማቀፋዊ ስታንዳርደዶች (ኤምፒኤስ፣ ቴስኮ፣ የአውሮፓ ጋፕና ግሎባል ጋፕ) የመሳሰለትን ቤንች ማርኮች በኤጀንሲው በኩል ለባለሀብቶችም ሆነ ለአውትግሮዎሮች የግንዛቤ

ማስጨበጫ ስራዎች ያለመሰራታቸውን፣ በተጨማሪም ለገበያው የሚቀርቡ የሆርቲካልቸር ምርቶች ከደንበኛው ፍላጎት አንፃር እንዲሁም ከየሀገሩ መመሪያ በተጣጣመ መልኩ የገበያውን መስፈርት/ ስታንዳርዶች የማያሟሉ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

110. የምግብ ደህንነት መስፈርቶችና አለማቀፋዊ ስታንዳርዶች (ኤምፒኤስ፣ ቴስኮ፣ የአውሮፓ ጋፕና ግሎባል ጋፕ) የመሳሰሉትን ቤንች ማርኮች በባለስልጠን መ/ቤቱ በኩል ለባለሀብቶችም ሆነ ለአውትግሮዎሮች እንዲያውቁት ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

111. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

112. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

113. ባለስልጣን መ/ቤቱ በሆልቲካልቸር የተሰማሩ ባለሀብቶች ኤክስፖርት የሚያደርጓቸው ምርቶች አለም አቀፍ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችን እና ስታንዳርዶችን (ኤምፒኤስ፣ቴስኮ፣ የአውሮፓ ጋፕና ግሎባል ጋፕ) የመሳሰሉትን ቤንች ማርኮች መሰረት የሚመረቱ ስለመሆናቸው ክትትል እንደማያደርግ እና ባለሀብቶችም ሆነ አውትግሮዎሮች እንዲያውቁት ያልተደረገ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከአልሚታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

114. የቬዥ ፍሩት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ባለስልጣን መ/ቤቱ የዩሮ ጋፕ አሰራርን ተከትለው እንዲሰሩ በየጊዜው ስልጠና እንደሚሰጣቸው፣ ክትትል እንደሚያደርግ የገለፁ ሲሆን የመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች የዩሮ ጋፕ አሰራርን በፕሮጀክት ቀርፀው እየተገበሩ መሆኑን እና ባለስልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክቱ እነደ አካል ሆኖ እየሠራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ የምርት ግብዓት በወቅቱና በሚፈለገው መጠን እንዲቀርብ ድጋፍና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤**

115. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

116. ለአትክልትና ፍራፍሬ ግብዓት አቅራቢ የሆነው የግብርና ግብዓት አቅራቢ ድርጅት(AISE) በዘርፉ የሚፈለገውን የምርት ግብዓት በሚፈለገው መጠን፣ አይነትና ወቅት የማቅረብ ችግር ያለበት መሆኑ፣ በተጨማሪም ኬሚካሎችን እና ግሪንሀውስ ፕላስቲክ የምርት ግብዓቶች የሚያስመጣ መሆኑ እንዲሁም የግብዓት አቅራቢ አስመጪዎች በቁጥር አነስተኛ በመሆናቸው እጥረት በተከሰተ ቁጥር እርስ በእርስ በመነጋገር ዋጋ የሚሰቅል መሆኑ እና ኤጀንሲው የግብዓት አቅርቦት ችግሮችን ለመቅረፍ የአገር ውስጥ አቅራቢዎችንና የሚመለከታቸውን በማስተባበር ድጋፍ ያለመስጠቱ ተገኝቶ ነበር፡፡

117. ባለስልጣን መ/ቤቱ በግብዓት አቅራቢነት የተሰማሩ ኩባንያዎች በማጠናከር ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በዓይነትና በመጠን እንዲቀርቡ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግና እጥረት በሚፈጠርበት ወቅት በማስተባበር ችግሩን የሚፈታበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

118. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

119. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

120. ባለስልጣን መ/ቤቱ በግብዓት አቅራቢነት የተሰማሩ ኩባንያዎች በማጠናከር ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በዓይነትና በመጠን እንዲቀርቡ ድጋፍና ክትትል እንደማያደርግ እንዲሁም እጥረት በሚፈጠርበት ወቅት በማስተባበር ችግሩን የሚፈታበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ የማያደርግ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ

አልሚዎች የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

121. ባለስልጣን መ/ቤቱ በግብዓት አቅራቢነት የተሰማሩ ኩባንያዎች በማጠናከር ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በዓይነትና በመጠን እንዲቀርቡ ድጋፍና ክትትል እንደማያደርግ እና እጥረት በሚፈጠርበት ወቅት በማስተባበር ችግሩን የሚፈታበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉን የደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

122. ጆይ ቴክ የተባለ እርሻ የሚገኘው በደብረዘይት ሲሆን ሀገር ውስጥ ከሚሸጡት /ኤክስፖርት/ ከሚያደርጉት ገበያ ጋር (MRL LEVEL OR LOW PHI) ሊስማሙ የሚችሉ ኬሚካል ያለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች ዕቅድ እና አፈፃፀም ክትትል የሚያደርግ መሆኑን በተመለከተ፣**

123. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

124. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዘርፉ የተሰማሩ በየወሩ የመስክ ጉብኝት በማድረግ የአምራቾችን አፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ የማያደርግ መሆኑ፣ እንዲሁም ቋሚና መደበኛ የሆነ የድጋፍና የክትትል ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣ እንዲሁም በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ችግሮች ለመለየት የተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች ተደርገው ለሚመለከተው አካል ያልቀረቡ መሆናቸው ተገኝቶ ነበር፡፡

125. በባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎችን ለመደገፍና ለመከታተል የሚያስችል ቋሚና መደበኛ የሆነ የድጋፍና የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እና በየጊዜው ከባለሀብቶች የሚነሱ ችግሮችን በመለየት መፍትሄ የሚያገኙበት አሰራር ሊኖር እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

126. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

127. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

128. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎችን ለመደገፍና ለመከታተል የሚያስችል ቋሚና መደበኛ የሆነ የእቅድና አፈፃፀም የክትትል ስርዓት ያልዘረጋ፣ ተግባራዊ ያላደረገ እንዲሁም በየጊዜው ከባለሀብቶች የሚነሱ ችግሮችን በመለየት መፍትሄ የሚያገኙበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

129. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎችን ለመደገፍና ለመከታተል የሚያስችል ቋሚና መደበኛ የሆነ የእቅድና አፈፃፀም የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ እና በየጊዜው ከባለሀብቶች የሚነሱ ችግሮችን በመለየት መፍትሄ የሚያገኙበት አሰራር ያልዘረጋ መሆኑን የደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

130. ባለፈው በ 2008 ዓ.ም በቁጥር ከ80 ባላነሱና በሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ልማት ከተሰማሩ ኩባንያዎች መካከል 24 ኩባንያዎች እቅድ እንዲያቀርቡ የተደረገ ሲሆን እቅድ ያቀረቡ ኩባንያዎች ጠቅላላ የመሬት ይዞታ 1130 ሄክታር መሆኑ፣በተክል እና በመሰረተ ልማት የተሸፈነ 318.712 ሄክታር ሲሆን ቀሪው 762. 38 ሳይለማ የቀረ እንደሆነ፣ከነዚህ ኩባንያዎች መሀከል 11 ኩባንያዎች በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፍ የተሰማሩና በድምሩ 811 ሄክታር መሬት ጠቅላላ ይዞታ ኖሯቸው ከዚህ ውስጥ ሄክታር መሬትን ብቻ አልምተው የቀረውን 688 ሄክታር መሬትን ሳይለሙ የቀሩ መሆኑን ከ 2008 ዓ.ም የመሬት አጠቃቀም ግምገማ ለማወቅ ተችሏል፡፡

**የባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ላኪ ድርጅቶችና ዩኒየኖች የውጪ ንግድ አፈፃፀም መከታተሉን በተመለከተ፤**

131. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

132. ባለሀብቶች በየአመቱ ኤክስፖርት የሚያደርጉትን የምርት መጠን ዕቅድ ለባለስልጣን መ/ቤቱ ቢያሳውቁም በእቅዳቸው መሰረት አድርገው ለውጭ ገበያ ማቅረብ አለመቻላቸውን ተገኝቶ ነበር፡፡

133. የአትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖርት ምርቶች በዋጋና በጥራት ተወዳዳሪነታቸውን ለማረጋገጥ ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ በመነሳት የተሻለ አመራረት፣ ጥራትና የምግብ ደህንነት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲኖር ከሆርቲካልቸር ማህበር ጋር በመተባበር የስልጠና እና የምክር አገልግሎት የሚሰጥበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ እና የኤክስፓርት አፈፃፀምና ለገበያው የሚቀርቡ የሆርቲካልቸር ምርቶች ከደንበኛው ፍላጎት አንፃር እንዲሁም ከየሀገሩ መመሪያ በተጣጣመ መልኩ በጥራት፣ በአይነትና በመጠን በወቅቱ ተሟልቶ እንዲቀርብ ኤጀንሲው የገዢዎችን ሀገራት የጥራት ፍላጎት ደረጃዎችን ለይቶ መረጃዎችን በማጠናቀር ለአምራች ላኪዎች አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

134. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት  የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

135. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

136. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ላኪ ድርጅቶች የውጪ ንግድ የምርት ሽያጭ የመንግስት ፖሊሲ፣ መመሪያና ደንብን ተከትለው መፈፀማቸውን እንዲሁም ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶች በተያዘው እቅድና በተፈፀመው ውል መሰረት መከናወናቸውን የሚከታተልበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ  ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና  ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች ፣ ከደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና ከጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

137. ባለስልጣን መ/ቤቱ የዘርፉን አማራጭ ገበያ ለማስፋት የአቅም ውስንነት እንዳለበት ከ 2009 ዓ.ም የባለስልጣን መ/ቤቱ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ  የአትክልትና  ፍራፍሬ  ምርት ማሸጊያ ማቴሪያሎች ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤**

138. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

139. ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ኤክስፖርት አገልግሎት የሚውል አገራዊ የፓኬጂንግ ስታንዳርድ (specification and standard) የሌለ መሆኑ እና ኤክስፖርት በሚፈልገው የጥራት ደረጃ ማምረት የሚችል ሀገራዊ ፋብረካዎች ያልተጠናከሩ መሆናቸው እንዲሁም ወደ ጅቡቲ የሚላከው የአትክልትና ፍራፍሬ አላላክና አስተሻሸግ ጥራት የጎደለው መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

140. ለሆርቲካልቸር ኤክስፖርት የሚሆኑ አገራዊ የፓኬጂንግ ስታንዳርድ (specification and standard) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

141. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት  የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

142. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

143. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሆርቲካልቸር ኤክስፖርት የሚሆኑ የምርት ማሸጊያ ማቴሪያሎች አገራዊ የፓኬጂንግ ስታንዳርድ (specification and standard) ደረጃቸውን የጠበቁና በወቅቱ የተዘጋጁ መሆናቸውን የሚከታተልበት፣ የሚቆጣጠርበት እና ድጋፍ የሚያደርግበት ስርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ  ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች፣ ከደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና ከጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከመጓጓዛቸው በፊት የሚቆዩበት የማቀዝቀዢያ፣ የትራንስፓርትና ሌሎችም የሎጀስቲክስ ፍላጎቶችን እንዲሟሉላቸው ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ፤**

144. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

145. የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በኢትዮጲያ አየር መንገድ ከፈተኛ የበረራ ፕሮግራም መዛባት(መዘግየት) የተነሳ ባለሀብቶች የሚልኳቸውን ምርቶች በወቅቱ ለደንበኞቻቸው

ስለማይደረስ ተጨማሪ ወጪዎች እና የጥራት ጉድለቶች የሚከሰቱ መሆኑና በተለይም ወደ አፍሪካ አገሮች ምርቶችን ለመላክ የአውሮፕላን በቂ ቦታ ባለመኖሩ ምርቶችን በተፈለገው መጠን ለመላክ ያልተቻለ መሆኑ፣

146. እንዲሁም በአርባ ምንጭ የምርት ማደራጃና ማቀዝቀዣ መጋዘን በኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ሎጂስቲክ አገልግሎት ድርጅት ግንባታው እንዲከናወን በ2005 ዓ.ም ስምምነት ላይ የተደረሰ ቢሆንም እስካሁን ግንባታው ያልተጀመረ መሆኑ እና የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በብዛት የሚመረትባቸው አካባቢዎች (አርቦ ምንጭ፣ ራያ ቆቦ፣ ምስራቅ ሀረርጌና ድሬዳዋ) የተሟላ የምርት ማደራጂያና ማከማቻ መጋዘን ያለመኖሩ ተገኝቶ ነበር፡፡

147. የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በብዛት የሚመረትባቸው አካባቢዎች (አርቦ ምንጭ ፣ ራያቆቦ፣ ምስራቅ ሀረርጌና ድሬዳዋ) የተሟላ የምርት ማደራጃና ማከማቻ መጋዘን ሊኖር እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

148. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት  የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

149. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

150. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በብዛት የሚመረትባቸው አካባቢዎች የተሟላ የምርት ማደራጃና ማከማቻ መጋዘን ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከመጓጓዛቸው በፊት የሚቆዩበት የማቀዝቀዣ፣ የትራንስፓርትና ሌሎችም የሎጀስቲክስ ፍላጎቶች እንዲሟሉ ለባለሀብቶች ድጋፍ እንዳላደረገ ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ  ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና  ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

**የባለስልጣን መ/ቤቱ  የገበያ መረጃዎችን  በማሰባሰብ፣  በማደራጀትና በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ተጠቃሚ መሆናቸውን በተመለከተ፤**

151. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

152. ባለስልጣን መ/ቤቱ የገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብና ለተጠቃሚዎች ከማዳረስ አንፃር የተሰራ ስራ ያለመኖሩ እና ዋና ዋና ገበያዎችን በማየት ባለሀብቶችን ለመደገፍ የሚያስችል የገበያ መረጃ ስርዓት ያልዘረጋና የገበያ ትስስር ያልተፈጠረ በመሆኑ አምራቾች የገበያ መረጃ የማጣት ችግር ያጋጠማቸው መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

153. ባለስልጣን መ/ቤቱ የገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብና ለባለሀብቶች ሊያሰራጭ እና ዋና ዋና ገበያዎችን በማየት ባለሀብቶችን ለመደገፍ የሚያስችል የገበያ መረጃ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

154. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት  የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

155. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

156. ባለስልጣን መ/ቤቱ የገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብና ለባለሀብቶች ያላሰራች እና ዋና ዋና ገበያዎችን በማየት ባለሀብቶችን ለመደገፍ የሚያስችል የገበያ መረጃ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢ.ትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና  ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች፣ ከደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና ከጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

157. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለኢ.ትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ በውጭ ሀገር የሚካሄዱ ስልጠናና አውደ ጥናት ኤግዚቢሽኖች ፕሮግራም ቦታውን፣ ጊዜውን ጠብቀው እንደሚያሳውቋቸው እና የሚጠይቋቸውን ድጋፍ እንደሚያደርጉላቸው የኢ.ትዮ ቬጅ ፍሩት የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

**የሀገሪቱን የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚመለከቱ መረጃዎች በዘመናዊ መልክ የሚደራጁበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤**

158. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

159. በባለስልጣን መ/ቤቱ  በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚረዱ የመረጃ መረብ (Web Site) ያልተዘረጋ መሆኑ፣ አዋጆች፣

ደንቦችና መመሪያዎች በየጊዜው የሚቀያየሩ ቢሆንም ኤጀንሲው በወቅቱ የማስተዋወቅ ስራ የማይሰራ በመሆኑ እና ለባለሀብቶች በወቅቱ ሳይገለፅ በመቅረቱ አገልግሎት ለማግኘት ወደ መ/ቤቱ (በተለይ ጉምሩክ ላይ) ሲሄዱ ተቀይሯል በማለት የሚጉላሉ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

160. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚረዱ የመረጃ መረብ (Web Site) ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ እና ዘርፉን የሚመለከቱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በየጊዜው ሲወጡም ሆነ ሲቀየሩ ባለስልጣን መ/ቤቱ በወቅቱ ለባለሀብቶች እንዲያውቁት ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

161. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት  የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

162. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

163. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚረዱ የመረጃ መረብ (Web Site) ያልዘረጋ፣ ተግባራዊ ያላደረገ እንዲሁም ዘርፉን የሚመለከቱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በየጊዜው ሲወጡም ሆነ ሲቀየሩ በወቅቱ ለባለሀብቶች እንዲያውቁት የማያደርግ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የህዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ  ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና  ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች፣ ከደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና ከጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

164. ባለስልጣን መ/ቤቱ የባለሀብቶችን አጠቃላይ የተሟላ መረጃ አደራጅቶ አለመያዙንም ከባለስልጣን መ/ቤቱ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ  ዘርፉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፤**

165. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

166. ባለስልጣን መ/ቤቱ በመሬት አሰጣጥ፣ በመሰረተ ልማት ማሟላት፣ በግብዓት አቅርቦት ዙሪያ በአጠቃላይ ዘርፉ የሚጠይቀውን አገልግሎት ከማቀላጠፍና ከማሳደግ ረገድ ያለው ቅንጅታዊ አሰራር የተጠናከረ ያለመሆኑ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ለመስራት በእቅድ የማይመራ መሆኑና ከኦሮሚያ ክልል ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ከሌሎች ክልሎች የተሻለ ቢሆንም መደበኛ የሆነ ግንኙነት የሌላቸው መሆኑ፣ እንዲሁም የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ፣ የሆርቲካልቸር ማህበርና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ቋሚ እና መደበኛ መድረክ ያለ ቢሆንም በታቀደው ጊዜ እየተካሄደ ያለመሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

167. ዘርፉ የሚጠይቀውን አገልግሎት ከማቀላጠፍና ከማሳደግ ረገድ ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር ሊኖረው እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

168. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

169. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

170. ባለስልጣን መ/ቤቱ ዘርፉ የሚጠይቀውን አገልግሎት ከማቀላጠፍና ከማሳደግ ረገድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር የሌለው መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሥራ ኃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

171. በክልሉና በአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች መካከል የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር ለመፍጠር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን የደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና ጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

172. ከባለስልጣን መ/ቤቱ የ2009 ዓ.ም የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ባለስልጣኑ ከክልሎች ጋር በቅንጅት/አላይንመንት/ ፈጥሮ የሚሰሩ ስራዎች አለማከናወኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

**የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤትን በተመለከተ፤**

173. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

174. የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶች፣ በምርምር ማእከላትና በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች እንዲጠናከሩ ከማድረግ አንፃር የተሰሩ ስራዎች ስለመኖራቸው በኦዲቱ ወቅት መረጃ አለመቅረቡ ተገኝቶ ነበር፡፡

175. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶች፣ በምርምር ማዕከላትና በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች እንዲጠናከሩ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

176. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

177. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

178. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶች በምርምር ማዕከላትና በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች እንዲጠናከሩ ድጋፍና ክትትል ያላደረገ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሥራ ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

179. የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ማዕከላትና የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች በክልሉ ስለመኖሩ እንደማያውቁ የደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

**የስትራቴጂክ እና ዓመታዊ ዕቅድ እና የዕቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ፤**

180. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

181. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ከ2003-2007 ዓ.ም የስትራቴጂክ ዕቅድ ያዘጋጀ ቢሆንም ከ2003 እስከ 2006 ዓ.ም የተዘጋጀው ዕቅድ የስራቴጂክ እቅድን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ አለመሆኑ ፣ የ2003-2006 ዓ.ም የዕቅድ አፈፃፀም በተለይ በውጪ

ንግድ በምርት መጠንም ሆነ በገቢ ከዕቅድ በታች መሆኑ፣ በአፈፃፀም ሪፖርት ላይ በየዓመቱ ተደጋጋሚ ችግሮች የሚገለፁ እና እነዚህን ችግሮች በየበጀት ዓመቱ መንስኤዎቻቸውን በመለየት የመፍትሄ እርምጃ የማይወሰድባቸው መሆኑ፣ እንዲሁም በእቅድ ዝግጅት ወቅት በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችንና የሚመለከታቸው አካላትን አሳታፊ ያደረገ ያለመሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

182. ባለስልጣን መ/ቤቱ ዓመታዊ ዕቅድ ሲያዘጋጅ የስትራቴጂክ ዕቅድን መሰረት ሊያደርግና በዕቅድ ዝግጅት ወቅት በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችንና የሚመለከታቸው አካላትን አሳታፊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

183. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድርጊት መረሃ ግብር አዘጋጅቶ አላከም፡፡

184. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

185. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዕቅድ ዝግጅት ወቅት በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችንና የሚመለከታቸው አካላትን አሳታፊ እንደማያደርግ የላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ የኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ የመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ የአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ የአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ፣ የኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና የሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሥራ ኃላፊዎች፣ የደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

186. በ2009 ዓ.ም ከሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ምርት 460.13 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚገኝ የገቢ ግብ ተጥሎ 271.24 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (58.95%) መሆኑ፡፡ ይህ አፈፃፀም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ1.53 በመቶ ቅናሽ ማሳየቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

187. እንዲሁም በ2009 ዓ.ም 83.53 ሺ. ቶን ፍራፍሬ ለማምረት ቢታቀድም 22.3 ሺ. ቶን የተመረተ ሲሆን አፈፃፀሙ በመቶኛ 27.34 % ሲሆን ከፍራፍሬ 28.44 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ይገኛል ተብሎ ቢታቀድም 8.36 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተገኘ ሲሆን አፈፃፀሙም 29.4% መሆኑ ታውቋል፡፡

188. በ2008 ዓ.ም 82.84 ሺ. ቶን ፍራፍሬ ለማምረት ቢታቀድም 18.02 ሺ. ቶን የተመረተ ሲሆን አፈፃፀሙ በመቶኛ 21.75 % ሲሆን ከፍራፍሬ 21.05 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ይገኛል ተብሎ ቢታቀድም 5.79 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተገኘ ሲሆን አፈፃፀሙም 27.51% መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

189. በአጠቃላይ በ2009 ዓ.ም 435.11 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚገኝ ግብ ተጥሎ 275.45 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (63.30%) መሆኑን ከባለስልጣን መ/ቤቱ መረጃዎች ለመመልከት ተችሏል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)

190. በባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የወጪ ንግድ አፈፃፀም ብቃትና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ተከናወኖ በቀረበው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

### 3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በየክልሉ የሚገኙ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምቹ የሆኑ መሬቶችን(ማሳዎችን) የለየ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረትና ምርት አያያዝ የአፈፃፀም ማንዋሎች ያዘጋጀ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የስትራቴጂክ እቅድ ያዘጋጀ መሆኑ፣
- የመሬት አቅርቦትን ለባለሀብቶች ለማመቻቸት የቢዝነስ ፕላን ግምገማ ማስፈጸሚያ ሰነድ መዘጋጀቱ፣

ታውቋል፡፡

### 3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው

- በባለስልጣን መ/ቤቱ ሊዘጋጅ የሚገባው ሁሉን አቀፍ የድጋፍ ማዕቀፍ የአትክልትና ፍራፍሬን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ዋና ዋና የድጋፍ አይነቶችን ማለትም በግብዓት አቅርቦት ድጋፍ፣ ከምርምርና መሰል ተቋማት በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ በተለይ በዘር ፍተሻ ማለማመድና ማባዛትን በተመለከተ፣ በመሬትና የመሰረተ ልማት አቅርቦት ድጋፍን በተመለከተ፣ በብድር አቅርቦት፣ በውጭ ምንዛሪ አቅርቦትና ዝውውር ድጋፍን በተመለከተ፣ በትራንስፖርት ዘርፍ ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ በተመለከተ፣ የአለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ለማሟላት የሚያግዝ የቴክኒክና የስልጠና ድጋፍን እንዲሁም ለዘርፉ የሚያስፈልጉ መረጃዎች አቅርቦት እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የአትክልትና

ፍራፍሬ ምርቶች በመጓጓዝ ሂደት ለሚያጋጥማቸው አደጋና ብልሽት ሊኖር ስለሚችል የዋስትና አቅርቦት ድጋፍ የመሳሰሉ የደድጋፍ ዓይነቶችን በዝርዝር በመለየት ድጋፍ የሚሰጠውን አካል ኃሊፊነት፣ ድጋፍ ሊገኝ የሚችልበትን ጊዜ፣ በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ ለማግኘት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር በመለየት ከአንድ መስኮት አገልግሎት(One window shopping) መሰረተ ሀሳብን የሚያመላክት ሁሉን አቀፍ የማበረታቻ የድጋፍ ማዕቀፍ ኤጀንሲው ሊያዘጋጅና በዘርፉ ሊሰማሩ ለሚችሉ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶች እንዲያውቁት የማይደረግ መሆኑ፣

- በአትክልትና ፍራፍሬ የተሰማሩ ባለሀብቶች የአዋጭነት ጥናት እንዲያቀርቡና የሚቀርቡ የአዋጭነት ጥናቶች ደረጃውን የጠበቀ፣ አዋጭነቱ አሰተማማኝ የሆነና ጥናቱ ሊተገበር የሚችል መሆኑ ተገምግሞ እንዲፀድቅ ያላደረገ መሆኑ፣
- በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች መሬት እና የመሰረተ ልማት አገሌግልቶች(መብራት ውኃ፣ ስልክ፣ መንገድ፣ ...ወዘተ) በወቅቱ እንዲሟላላቸው አለመደረጉ፣
- አትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የብድር አገልግሎቶች የሚያገኙበት አሰራር ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- የአትክልትና ፍራፍሬ ልማቶችን በሰው ኃይል እንዲጠናከሩ በባለስልጣን መ/ቤቱ ድጋፍና ክትትል የሚደረግበት አሰራር ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ለክላስተር የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለሉ ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች በወቅቱ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በውሉ መሰረት የማይሰሩ ባለሀብቶች ላይ እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር አለመዘርጋቱ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በሆርቲካልቸር ልማት የሚሰማሩ አውትግሮዎሮች እንዲደራጁ ሊያደርግ እና አውትግሮዎሮቹና አምራቾች በቂና ተከታታይነት ያለው የክህልት ስልጠናዎች እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል አለማድረጉ፣
- በተከታታይ የቴክኖሎጂ ማስረፅ (የሆርቲካልቸር ስራ ዘርፍ በቂ ክህሎትና የስራ ተነሳሽነት በማዳበር ሙያዊ ድጋፍ ከመስጠት አንፃር) የአቅም ግንባታ ድጋፎች

በተጠናከረ መልኩ ለባለሀብቱም ሆነ ለአውትግሮዎሩ እንደማይሰጡ እና የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረትና ምርት አያያዝ የአፈፃፀም ማንዋሎች ቢዘጋጁም ተግባራዊ አለመደረጋቸው፣

- የምግብ ደህንነት መስፈርቶችና አለማቀፋዊ ስታንዳርዶች (ግሎባል ጋፕ) ቤንች ማርኮች በባለስልጣን መ/ቤቱ በኩል ለባለሀብቶችም ሆነ ለአውትግሮዎሮች እንዲያውቁት አለመደረጉ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በግብዓት አቅራቢነት የተሰማሩ ኩባንያዎች በማጠናከር ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በዓይነትና በመጠን እንዲቀርቡ ድጋፍና ክትትል እንደማያደርግ እና እጥረት በሚፈጠርበት ወቅት በማስተባበር ችግሩን የሚፈታበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣
- በባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎችን ለመደገፍና ለመከታተል የሚያስችል ቋሚና መደበኛ የሆነ የድጋፍና የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ እና በየጊዜው ከባለሀብቶች የሚነሱ ችግሮችን በመለየት መፍትሄ የሚያገኙበት አሰራር የሌለ መሆኑ፣
- የአትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖርት ምርቶች በዋጋና በጥራት ተወዳዳሪነታቸውን ለማረጋገጥ ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ በመነሳት የተሻለ አመራረት፣ ጥራትና የምግብ ደህንነት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲኖር ከሆርቲካልቸር ማህበር ጋር በመተባበር የስልጠና እና የምክር አገልግሎት የሚሰጥበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ እና የኤክስፓርት አፈፃፀምና ለገበያው የሚቀርቡ የሆርቲካልቸር ምርቶች ከደንበኛው ፍላጎት አንፃር እንዲሁም ከየሀገሩ መመሪያ በተጣጣመ መልኩ በጥራት፣ በአይነትና በመጠን በወቅቱ ተሟልቶ እንዲቀርብ በባለስልጣን መ/ቤቱ የገዢዎችን ሀገራት የጥራት ፍላጎት ደረጃዎችን ለይቶ መረጃዎችን በማጠናቀር ለአምራች ላኪዎች አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣
- ለሆርቲካልቸር ኤክስፓርት የሚሆኑ አገራዊ የፓኬጂንግ ስታንዳርድ (specification and standard) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በብዛት የሚመረትባቸው አካባቢዎች የተሟላ የምርት ማደራጃና ማከማቻ መጋዘን አለመኖር፣

- ባለስልጣን መ/ቤቱ የገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብና ለባለሀብቶች የማያሰራጭ መሆኑ እና ዋና ዋና ገበያዎችን በማየት ባለሀብቶችን ለመደገፍ የሚያስችል የገበያ መረጃ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚረዱ የመረጃ መረብ (Web Site) አለመዘርጋቱን እና ዘርፉን የሚመለከቱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በየጊዜው ሲወጡም ሆነ ሲቀየሩ በወቅቱ ለባለሀብቶች እንዲያውቁት እንደማያደርግ
- ዘርፉ የሚጠይቀውን አገልግሎት ከማቀላጠፍና ከማሳደግ ረገድ ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር የሌለው መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶች፣ በምርምር ማዕከላትና በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች እንዲጠናከሩ ድጋፍና ክትትል አለማድረጉ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ዓመታዊ ዕቅድ ሲያዘጋጅ የስትራቴጂክ ዕቅድን መሰረት ያላደረገና በዕቅድ ዝግጅት ወቅት በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችንና የሚመለከታቸው አካላትን አሳታፊ አለማድረጉ፣

እስከአሁን መኖሩ ታውቋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

191. በመጀመሪያው የክዋኔ ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑት የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡

192. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ባልተስተካከሉና የእርምት እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብርም ተዘጋጅቶ ለመ/ቤታችን መላክ አለበት፡፡

በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን፣ እና በናሙና የታዩት የክልልና የዞን ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ፣የአትክልትና ፍራፍሬ ኩባንያዎች እና ማህበራት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡